INTERME

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS
AUTHORITY
A.A. KAIITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

የውስጥመጻጻፊ

ቁጥር፡ ም/ሥ/የአድ/00116/10
ቀን፡ 24/01/2010

ለ፦ ሁሉም ክሊራንስ ዩኒቶች
ለ፦ ጉምሩክ ስነ ስርዓት አፈፃፀም የስራ ሂደት
ለ፦ ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት
ለ፦ ደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት
ለ፦ ኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን የጉ/ስ/ስ/አ ስራ ሂደት
ለ፦ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉ/ስ/ስ/አ ስራ ሂደት

ከ፦ ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
<u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

Azizew Chanie
Customs Affair Deputy
Manager

የጉምሩክ ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ በደብዳቤ በቁጥር 3.0/50/10 መስከረም 20/2010 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የመገናኛ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ደረጃቸውን ያልጠበቁ የሞባይል ስልኮች በኔቶርኩም ሆነ በሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚዎች ላይ የአገልግሎት ጥራት መጓደል እንዳያስከትሉና በኮንትሮባንድ የሚገቡ ተመሳስለው የሚሰሩ እና ያልተመዘገቡ የሞባይል ስልክ ቀፎዎች መንግስት ከገቢ ዕቃዎች ቀረጥ የሚሰበስበውን ገቢ በማሳጣት በአስመጪዎች መካከል አግባብነት የሌለው የገበያ ውድድር እንዳያስከትሉ በማሰብ የሞባይል ቀፎዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 2/2009 ማውጣቱን ገልፆ በአንቀጽ አስራሁለት በንዑስ አንቀጽ አንድ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሞባይል ስልክ ቀፎ ምዝገባ ስርዓቱ ላይ በሚሰጠው የተወሰነ የተደራሽነት መብት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሞባይል ስልክ ቀፎው አስቀድሞ የተሰጠውን ምዝገባ እና ፈቃድ በማረጋገጥ እና የገቢ ዕቃዎች ቀረጥ የተከፈለበትን ደረሰኝ ቁጥር በማስገባት ሞባይክ ስልክ ቀፎው ከጉምሩክ የመቅረጫ ጣቢያዎች እንዲወጣ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት እና በተቀመጠው መመሪያ መሰረት ስራውን ለመስራት አንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች ችግር ያጋጠማቸው ስለሆነ ወደ ተግባር ለመግባት የተቸገሩ መሆኑን አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም አገልግሎቱ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ሲመቻቹ በተላከው መመሪያና አሰራር መሰረት አገልግሎቱ እንዲሰጥ እና ቁጥጥር እንዲደረግ እያሳሰብኩ የተላከውን 11 ገጽ ደብዳቤ በአባሪነት አያይዘን ልከንላችኋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለም/ስራ አስኪያጅ /ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ዘርፍ/
  <u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ቁጥር 3-ህ/50/10
Ref. No
ቀን 20 መስከረም 2010
Date

**ጉዳዩ፡- <u>የሞባይል ስልክ ቀፎዎች መዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን ይመለከታል፤</u>**

የመገናኛኛ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ደረጃቸውን ያልጠበቁ የሞባይል ስልኮች በኔትወርኩም ሆነ በሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚዎች ላይ የአገልግሎት ጥራት መጓደል እንዳያስከትሉና በኮንትሮባንድ የሚገቡ፣ ተመሳስለው የሚሰሩ እና ያልተመዘገቡ የሞባይል ስልክ ቀፎዎች መንግስት ከገቢ ዕቃዎች ቀረጥ የሚሰበስበውን ገቢ በማሳጣት፣ በአስመጪዎች መካከል አግባብነት የሌለው የገበያ ውድድር እንዳያስከትሉ በማሰብ የሞባይል ቀፎዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 2/2009 አውጥቷል።

በዚህ መመሪያ አንቀፅ አስራሁለት ንኡስ አንቀፅ አንድ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሞባይል ስልክ ቀፎ ምዝገባ ስርዓቱ ላይ በሚሰጠው የተወሰነ የተደራሽነት መብት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሞባይል ስልክ ቀፎው አስቀድሞ የተሰጠውን ምዝገባ እና ፈቃድ በማረጋገጥ እና የገቢ ዕቃዎች ቀረጥ የተከፈለበትን ደረሰኝ ቁጥር በማስገባት የሞባይል ስልክ ቀፎው ከጉምሩክ የመቅረጫ ጣቢያዎች እንዲወጣ የማድረግ ሀላፊነት እንዳለበት ተገልጿል።ሆኖም በተቀመጠው መመሪያ መሰረት ስራውን ለመስራት አንዳንድ ቅ/ፅ/ቤቶች ችግር ያጋጠማቸው ስለሆነ ወደ ተግባር ለመግባት የተቸገሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤

<u>በዚሁ መሰረት፡-</u>

1. **በሞባይል ስልክ ቀፎ ገጣጣሚ ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ ለመገጣጠም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የሞባይል ቀፎ መሣሪያ አካላት፣**

    ሀ/ በሀገር ውስጥ ለመገጣጠም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የሞባይል ስልክ ቀፎ አካላት ሥራቸው ያልተጠናቀቀ ሲሆን የቀፎው መለያ ቁጥር በመገኛኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በተዘጋጀው ሥርዓት የሚመዘገቡ ይሆናሉ።

    ለ/ የሞባይል ስልክ ቀፎ ገጣጣሚ ፋብሪካዎች የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ \ሀ\ ተጠቃሚዎች ከሆኑ የሞባይል ስልክ ቀፎ አካላት በሞባይል ስልክ ቀፎ ገጣጣሚ ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ ለመገጣጠም ሲመጡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ \ሀ\ መመሪያ ቁጥር 45/2008 መሰረት



ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia